**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ. ም.)**

**የአዋሳው የወያኔ ጉባኤ እርስ በርስ አነታረካቸው፤መለስ ከጀሌቹ ተነጥሎ በልዩ ጥበቃ ተከብቦ ከረመ፤መለስና አርከበ በመቀሌ ተጨቃጨቁ ተባለ፤የትግራይ ተምቤን አውራጃ ህዝብ መለስን ተቃወሙ፤በቤተ- መንግስት አዲስ ጦር ለጥበቃ ተመደበ፤አንድ የወያኔ አባል ረሀቡን በፊልም ቀርፆ በማቅረቡ በደህንነቶች ታፍኖ የደረሰበት አለመታወቁ፤ ረሀቡ 144 ወረዳዎችን አዳረሰ፤በሱማሌ ክልል ህዝቡ በርሀብ መሞት ጀመረ፤የሞቱት ከብቶች ተሰብስበው እንዲቃጠሉ ተደረገ፤የሲ .ኤን. ኤን. ቻናል ጋዜጠኞች ኦጋዴን የተከሰተውን የረሀብ ትርኢት ቀረፁ፤አልጀዚራም በአካባቢው ደረሰ ተባለ፤ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣናት ቁጥጥር ስር ወደቀ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ............**

ለ3 ቀናት ሲካሔድ የሰነበተው የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ ሲታመስና ሲታሽ ቆይቶ እነመለስን መልሶ በመሾም ተጠናቀቀ::

በአዋሳ ከተማ በስውር ደህንነትና በጦር ሀይል ተወጥሮ ሲካሄድ የሰነበተው ይኸው የወያኔ ጠቅላላ ጉባዔ ረቡዕ መስከረም 7 ቀን 2001 ዓ. ም. እረፋዱ ላይ የተጠናቀቀ ሲሆን አንድም ሹም ሽር ሳያደርግ መለስ ዜናዊን ሊቀ መንበር አዲሱ ለገሰን ምክትል ሊቀመንበር አድርጎ በማፅደቅ ስብሰባው ተጠናቅቆዋል::

ከመስከረም 5 እስከ መስከረም 7ቀን 2001 ዓ. ም. ለ3 ቀናት በአዋሳ ከተማ በሲዳማ ባህል አዳራሽ ሲካሄድ የሰነበተ ሲሆን ወጣት የወያኔ አባሎች እነ መለስን በጥያቄ ቢያጣድፉዋቸውም አስቀድመው ይሄ ሊመጣ እንደሚችል ተዘጋጅተውበት ስለነበር በማስፈራራት የተነሱትን ጥያቄ-ች በሙሉ መምከናቸውን ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በተለይ ደኢህዴን የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት አባሎች «የግለሰብ አምባገነንነት እየሰፈነ ስለሚመጣ የስልጣን ጊዜ ገደብ ሊቀመጥለት ይገባል »በማለት ጥያቄና ሀሳብ ያቀረቡ ቢሆንም ወትሮም ለራሳቸው የሚጨነቁት እነ መለስ ዜናዊ ለተጠየቁት ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ አድበስብሰው እንደገና መልሰው እራሳቸው ስልጣኑን ለመያዝ እንደቻሉም ይኸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

በልዩ ጥበቃ ተወጥሮ የሰነበተው መለስ ዜናዊ ተመልሶ እንዲመረጥ እና ቦታው ከህወሀት እጅ እንዳይወጣ አስቀድሞ ለተሰብሳቢቹ በስልክና በአካል ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ የተሰጣቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ የተማሩ ናቸው የተባሉ የወያኔ የማዕከላዊ ኮሚተ አባላት «የአንድ ግለሰብ ስልጣን ላይ ብዙ ጊዜ መቆየት ችግር ሊፈጥር ስለሚችል በዴሞክራሲያዊ መንገድ መልቀቅና ለሌላ መስጠት አለበት»በማለት ያሳሰቡ ቢሆንም ሀሳባቸው መክኖ መቅረቱንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ስብሰባው ተጀምሮ አስኪጠናቀቅ ድረስ በጭቅጭቅ የሰነበተ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ መለስና አዲሱ በነበሩበት ስልጣን እንዲቀጥሉ የተደረገ ሲሆን፤ በርካቶች የማዕከላዊ ኮሚቲ አባላት ግን በምርጫው  ድምጽ አሰጣጥ ላይ ችግር ይፈጥሩና ያዋርዱናል በሚል ስጋት ስለገባቸው እያንዳንዱ አባል ፊት ለፊት እጃቸውን እንዲያወጡ መደረጉንና ድምፅ ያልሰጡ አባሎች ስማቸው በምስጢር እየተመዘገበ ማስፈራራት ሲደርስባቸው እንደነበረም ዘገባው አስረድቶዋል።

የካድሬዎቹ  ድርጊት ያስቆጣው መለስ የውሸት ምርጫ ተደርጎ መመረጡን ካረጋገጠ በሁዋላ በአሸናፊነት ስሜት ጠረጴዛውን ደጋግሞ በቡጢ እየቀጠቀጠ ሲያስፈራራ እንደነበረም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ  አስረድቶዋል።

በዚሁ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲገኙና የየበኩላቸውን ተሳትፎ እንዲያደርጉ የተጋበዙ ከውጭ ሀገር የመጡ የኮሚዩኒቲ ተጠሪች በስብሰባው ላይ የተገኙ ቢሆንም በመክፈቻው ላይ ብቻ ለ30 ደቂቃ እንዲገኙ ከተደረገ በሁዋላ መልሰው ከአዳራሹ እንዲወጡ መደረጋቸውንና በዚህም ብዙቹ ከውጭ ሀገር የመጡት ሰች በነመለስ ድርጊት ተበሳጭተው ወደ የመጡበት ሀገር መመለሳቸውንም ዘገባው አብራርቶዋል።

ይህ እርምጃ የተወሰደው በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ ንትርክና ውዝግብ ይፈጠራል ይህ ደግሞ ገመናችንን ያጋልጥብናል ብለው እነመለስ ስለሰጉ አስቀድመው  አባርረዋቸው ዝግ ስብሰባ ማድረጋቸው የግለሰቦቹን አምባገነንነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነው ብሎዋል።

መለስ ዜናዊ የገዛ ራሴ ናቸው የሚላቸው ባለስልጣናት እንኩዋን ሳያውቁ  ከዚህ ቀደም በጥበቃ ላይ ያልነበሩ በልዩ ኮማንዶች ታጅቦ ለ3ቀናት ብቻውን  የከረመ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከህወሀቶችም ጭምር ከፍተኛ ትችትና ወቀሳ ሲሰነዘርበት እንደነበረም ዘገባው አስረድቶዋል።

ሕዝቡን መፈናፈኛ ያሳጣ ጥበቃ ሲደረግ የሰነበተው የአዋሳ ከተማው ስብሰባ  ያለ አንዳች ለውጥ የተጠናቀቀ ቢሆንም በስብሰባው ላይ በነበረው ውዝግብ ግን ከፍተኛ ፍርሀትና ስጋት በነመለስ ዘንድ ፈጥሮባቸው እንደነበረና በደህንነትና በልዩ ጥበቃ ክፍሎች አማካኝነት እያስፈራሩና እያስደነገጡ ባሰቡት መንገድ ያጠናቀቁ ቢሆንም ተለኩሶ የነበረው እሳት ግን ውሎ አድሮ ችግር መፍጠሩ አይቀሬ መሆኑን የሚያመላክት ነው ያለው የደረሰን ዘገባ መለስ የራሱን ጀሌች እንኩዋን ባለማመኑ ለብቻው በልዩ ጥበቃ ተነጥሎ መክረሙን ዘገባው አብራርቶዋል።

ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 10:30 ከመስከረም 5 ቀን እስከ መስከረም 7 ቀን 2001 ዓ. ም. ድረስ ሲነታረኩበት  የነበረው ይኸው የወያኔ ጠቅላላ ጉባዔ ባለ 10 ነጥብ ሀሰተኛና ማስመሰያ ዲስኩር ብቻ የአቁዋም መግለጫ በማውጣት ቢጠናቀቅም ወጣት ካድሬቹ ግን ተከፍተውና አኩርፈው እንደወጡ ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።ለማስመሰልና ዲሞክራሲያዊ ነው ለማሰኘት 3 ዕጩ-

ችን ለሊቀመንበርነት አቅርበው የነበረ ሲሆን እነዚህ ዕጩ የተባሉት መለስ ዜናዊ - ከህወሀት፤አባዱላ ገመዳ -ከኦህዴድ እና አዲሱ ለገሰ -ከብአዴን እንደነበሩና ሁለቱ ከምርጫው እራሳችንን አግልለናል እንዲሉ ተደርጎ ምርጫው በመለስ አሸናፊነት ተጠናቀቀ ተብሎ መታወጁም ታውቋዋል::

ወያኔ በምርጫ ሙሉ በሙሉ በተሸነፈበት ወቅት በአስተዳደሩ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ አጎለብታለሁ ብሎ ህዝቡን ለማታለል ቃል የገባ ቢሆንም ቃልና ተግባር ለየቅል ሆነውበት ዛሬም የግለሰብ አምባገነንነትን አንግሶና የመልካም አስተዳደር ፈፅሞ የማይታሰብና ወያኔ እስካለ ድረስ ፍፁም እንደማይሆን ያረጋገጠበት ነው ያለው የደረሰን ዘገባ የሴቶችን ተሳትፎ እናጠናክራለን እያለ መለስ ጭምር ሲደሰኩር የነበረ ቢሆንም ሀቁ ግን ፍፁም ውሸት መሆኑን ያሳየ ነው ሲል ዘገበው አብራርቶዋል::

በአዋሳው በተደረገው ጉባዔ ተብዬ ላይ ወያኔ ከመረጣቸው 39 የስራ አስፈፃሚ አባላት መሀከል አንድ ብቻ ሴት ማስቀመጡ ስርዓቱ በቃል ከመናገር ባለፈ የሚፈፅመው አንዳችም ነገር እንደሌለ አመላካች ነው ሲል ዘገባው አስረድቶዋል::

ከወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ አስቀድሞ ህወሀት በመቀሌ፤ ብአዴን በባህርዳር ፤ኦህዴድ በአርሲ፤ደኢህዴን በወላይታ ሶዶ ከተሞች የተናጠል ጉባኤያቸውን ያካሄዱ ሲሆን፤ ብአዴን ምክትል ሊቀመንበሩን ተፈራ ዋልዋን አንስቶ ደመቀ መኮንን የተባለ ሌላ አፍለኛ ካድሬ ከመሾሙ በስተቀር ሌሎቹ የወያኔ ተቀጽላች ግን ሁሉም በፊት የነበሩዋቸውን መሪች መልሰው በመምረጥ የተጠናቀቀ መሆኑም ታውቆዋል::

የመለስን መከፋት አይተው የሚያለቅሱ፤ ፈገግታውን ሲያዩ ጮቤ የሚረግጡ ሆድ አደር ባለስልጣናት ከህዝብና ከሀገሪቱ ላይ ዘርፈው ያግበሰበሱት ሀብት ችግር እንዳይፈጥርባቸው ሲሉ ብቻ የመለስን ቃል እንደገደል ማሚቶ እያስተጋቡ ሳይልኩዋቸው ወደየት ሳይጠሩዋቸው አቤት በማለት እንደ ለማዳ ውሻ ጭራቸውን እየቆሉ የኖሩና አሁንም እየኖሩ ያሉ ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ይኸው ፀረ - ህዝብ ድርጅት ተብዬ ያለ አንዳች ለውጥ ጉባኤውን ቢያጠናቅቅም ከመቀሌ እስከ አዋሳ ድረስ ግን ፈታኝና አንገብጋቢ ጉዳዮች ተነስተው እነ መለስን ሲያስጨንቁ እንደሰነበተ ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ህወሀት በመቀሌ ባደረገው የተናጠል ሰብሰባ ላይ አርከበ እቁባይ እና መለስ ዜናዊ ሲጨቃጨቁ እንደነበርና እነ ስብሀት ነጋ በሽምግልና ነገሩን እያበረዱት እንደነበር ከመቀሌ የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም በፓርቲው ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ዙሪያ ላይ በጉባኤው ላይ የተገኙት ጥቂት ወጣት ካድሬች«አባቶቻችንና ወንድሞቻችን መስዋዕትነት የከፈሉት የአንድ ግለሰብ አምባገነንነት ለማስፈን ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን

ለመገንባት ነበር፡፡አሁን ግን እያየንና እየተደረገ ያለው ፍፁም የግለሰብ አምባገነንነት የማዋቀር ስራ ስለሆነ ቤቱ በዚህ ዙሪያ አስተያየት ሊሰጥበትና ሊመክርበት ይገባል» በማለት ከረር እና መረር ያለ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ፤አርከበ እቁባይም የወጣት ካድሬቹን ሀሳብ በመደገፍ ተጨማሪ አስተያየቶችን በማከሉ በመለስና በአርከበ መሀከል ከፍተኛ ጭቅጭቅ ተከስቶ እንደነበር ከመቀሌ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ከስብሰባው ማጠቃለያ በሁዋላ ለአንድ ቀን በተደረገው የህወሀት ባለስልጣናት ግምገማ ላይ አርከበ እቁባይ አልገኝም በማለት አቁዋም ወስዶ የነበረ ቢሆንም እነ ስብሀት ነጋ በጀመሩት የሽምግልና ተግባራቸው አግባብተው ወደ ግምገማው እንዲገባ ቢደረግም አንዲትም አስተያየት ሳይሰጥ እንደወጣም ይኸው ዘገባ ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ከትግራይ ህዝብ ጭምር ድጋፍ ያጣው መለስ ጉባኤውንና ግምገማውን ካጠናቀቀ በሁዋላ ጳጉሜ 3 ቀን 2000 ዓ. ም. በተምቤን አውራጃ እየተዘዋወረ ህዝቡን ለማነጋገር እና ድጋፍ ለማሰባሰብ ሞክሮ የነበረ ቢሆንም ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰበት የደረሰን ዘገባ ገልፆ የተምቤን ህዝብ በምሬት «መስዋዕትነት የከፈልነው ለናንተ ትከሻ ማሳበጫ ሳይሆን አምባገነኑን ደርግ አውርደን ለሁሉም በእኩልነት የምትሆን ሀገር ለመመስረት ነበር፡፡ዛሬ ግን ያ ሁሉ ድካምና ልፋታችን መና ቀርቶ ለርሀብና ለእርዛት ተዳርገን እንገኛለን፡፡ አንዲትም ልማት ሳናይ 17 ዓመት ሙሉ አስቆጥረናል፡፡ታዲያ ይህ ነው የኛ ድካምና ልፋት ውጤቱ ?»በሚል መለስን ሲያስጨንቁት መለስም ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ ጠይቆ በቅርቡ እንደሚስተካከልላቸው ቃል የገባ ቢሆንም ተዝናንቶ ገብቶ አቀርቅሮ መውጣቱን የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ደኢህዴን የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ፓርቲ በወላይታ ሶዶ ከተማ ባደረገው ስብሰባ ላይ «ያስመዘገብነውን አኩሪ የልማት ተግባር ወደፊትም እንድንቀጥልበት ተግተን ልንሰራ ይገባናል » እያለ የመለስ ተላላኪ ደሳለኝ ኃለማሪያም የተባለው ካድሬ ሲወተውት ከተሰብሳቢቹ አንደኛው «እናንተ ልማት አስመዝግበናል እያላችሁ ትነግሩናላችሁ፡፡ በዚህች ደቂቃና ሰከንድ ግን ብዙ ህዝብ በርሀብና በጠኔ እየረገፉ ናቸው፡፡ይህንንም በተጨባጭ አርባ ምንጭ አካባቢ ተገኝቼ በፊልም ቀርጬ ያመጣሁትን መመልከት ትችላላችሁ»በማለት ተዘዋውሮ ቀርፆ ያመጣውን የረሀብተኞችና የሙዋቾች አስከሬን ምስልና ህዝቡን የነጋገረበትን ፊልም በአዳራሹ ውስጥ ለተሰበሰቡት ካድሬች በማሳየት ልማት አስመዝግበናል እያለ ሲወተውት የነበረውን የመለስን አሽከር ደሳለኝ ኃይለ ማሪያም እና ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣናትን ያስደነገጠ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

በወቅቱ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩ በርካታ የደኢህዴን የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ቡድን አባላት በድርጊቱ በማዘን ሲያጉረመርሙና ሀሳባቸው ሊቀየር መሆኑን የተረዳው ደሳለኝ ኃይለማሪያም «ይህንን ፊልም ከየት ቀርፆ እንዳመጣ ይጠየቃል ፡፡አሁን ያየናቸው የኛ

ክልል ሰች አይደሉም ። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜ ሳናባክን ወደ ቀጣዩ ፕሮግራማችን እንግባ » በማለት ቢለፍፍም ተሰብሳቢቹ በማመጻቸው በግዳጅ ለሻይ እረፍት እንዲወጡ መደረጋቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

ከጥቂት ሰዓት ቆይታ በሁዋላ ተመልሰው ወደ ስብሰባ አዳራሹ ውስጥ ሲገቡ ዛቻና ማስፈራሪያ የታከለበት ንግግር ከመድረክ ላይ ደሳለኝ ኃይለማሪያም እና ከተሰብሳቢቹ መሀከል ደግሞ ካሱ ኢላላ በመረባረብ ተሰብሳቢቹን በማስደንገጥ ወደ ቀጣይ ፕሮግራም ያለፉ መሆኑን የገለጸው የደረሰን ዘገባ ጳጉሜ 4 ቀን 2000 ዓ. ም. ረፋዱ ላይ ጉባኤው ተጠናቅቆ ሁሉም ወደየቤቱ የተመለሰ ሲሆን የረሀቡን አስከፊነትና አሳሳቢነት ያጋለጠው ግለሰብ ግን በደህንነት ተጠልፎ ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዱን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

በወቅቱ በስብሰባው ላይ የነበሩ አንድ ግለሰብ እንደገለጹት ከሆነ ማንነታቸውን ያላወቅናቸው 3 ግለሰቦች ነጭ ላንድ ክሩዘር ኮድ 2 የሆነ መኪና ይዘው መጥተው ስብሰባው ሊጠናቀቅ ጥቂት ደቂቃች እንደቀሩት «ልናነጋግርህ እንፈልጋለን» በማለት ከአዳራሹ አስጠርተው ወደ አዲስ አበባ እንደወሰዱት ገልፀው የተደበቀውን ሀቅ በማውጣቱ ሊወደስና ሊሸለም ሲገባው የመከራን ፅዋ ለመጋት ደብቀውና አፍነው መውሰዳቸው የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉም ገልፀዋል።

ኃይለማሪያም ደሳለኝ የተባለው የወያኔ ባለስልጣን የደቡብ ክልል ፕሬዝደንት ሆኖ በሚሰራበት ወቅት በአዋሳ አቅራቢያ ሎቄ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ህዝቡ የዘንባባ ቅጠልና የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዞ የመብት ጥያቄ ለማቅረብ ሰላማዊ ሰልፍ በወጣበት ወቅት ለመከላከያና ለፌዴራል ፖሊስ በሰጠው ትዕዛዝ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ሰች እንዲገደሉ ካደረገ በሁዋላ መለስ ከቦታው አንስቶ አማካሪ አድርጎ ሾሞ ያመጠው ሲሆን ደኢህዴን የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ስራ አስፈፃሚች ግን ግለሰቡ በሰራው ተደጋጋሚ ጥፋት ምክንያት ከፓርቲው ሊቀመንበርነት ላልተወሰነ ጊዜ አግደውት የነበረ ቢሆንም በቅርቡ በመለስ ትዕዛዝ ወደ ሊቀመንበርነቱ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑንም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

ሌላው ኦህዴድ የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት በበኩሉ በአርሲ ከተማ ውስጥ ባደረገው ስብሰባ ላይ ከፍተኛ የሀሳብ ሽኩቻ ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን እነ አባዱላ ገመዳ አርፋችሁ ተቀመጡ ያልናችሁን ብቻ ተቀበሉ እያሉ ተሰብሳቢ ካድሬቹን እያስፈራሩ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም አንድ ወጣት ካድሬ «የዛሬ ሶስት ዓመት የኛ ፓርቲ መቼ ነው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የሚይዘው ብለን አንስተን ነበር።አሁንም ያለምንም ለውጥ እዛው ነው ያለነው ይሄ እስከመቼ ይቀጥላል?»በማለት ጥያቄ ቢያቀርብም የመለስ አሽከር የሆኑት አባዱላ ገመዳና ግርማ ብሩ ተረባርበው

ጥያቄው ወቅቱን ያላገናዘበ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜ ባናጠፋ ጥሩ ነው በሚል አድበስብሰው ያለ አንዳች ምላሽ እንዳለፉት የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ብአዴን የተባለው ድርጅት ውስጥም በተመሳሳይ የተለያዩ ጥያቄች የተነሱ ቢሆንም ነባር ካድሬ የሆነውን ተፈራ ዋልዋ ከምክትል ሊቀመንበርነት እንዲነሳ ሲጠየቅ «ያጠፋሁት ምን እንደሆነ አላወቅኩም፤ ለውጥ ከሆነ ሁላችንም ነው መቀየር ያለብን፡፡ለምን እኔ ብቻ ተነጥዬ እንድነሳ ተደረገ »በማለት ቢወተውትም መለስ ዜናዊ ለእነ አዲሱ ለገሰ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ከስልጣኑ ተነስቶ በምትኩ ደመቀ መኮንን የተባለው ሌላው የወያኔ ካድሬ መመረጡን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡ በወቅቱ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ በርካታ ካድሬች በድርጊቱ በመገረም የተፈራን ሀሰብ በመደገፍ ቢከራከሩም የአለቃውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ቀና ደፋ የሚለው አዲሱ ለገሰ በራሱ ቡድን በኩል በሰራው ፖለቲካዊ ስራ ለማሸነፍና የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ እንደቻለ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በሌላ በኩል መለስ ዜናዊ የራሱን ሹመኛ ባለስልጣናት ባለማመኑ በቅርቡ የቤተመንግስት ዙሪያ ጥበቃ ልዩ ኮማንዶ በድብቅ በሰለጠኑ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች በሆኑ ወታደሮች መቀየራቸውን የቤተመንግስት ምንጮች ገለፁ፡፡

እንደ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ የት ማሰልጠኛ ሰልጥነው እንደመጡ ያልታወቁት አንድ ሻለቃ ወታደሮች በቤተመንግስት ግቢ ለጥበቃ የተመደቡ ሲሆን ፤ቀድሞ ቤተ መንግስቱን ሲጠብቁ የነበሩት ወታደሮች ገሚሶቹ ወደ ሌላ ቦታ ሲዛወሩ ገሚሶቹ ደግሞ የቤተ መንግስቱን የውጭ ክፍል እንዲጠብቁ መመደባቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የቤተ መንግስት ጥበቃ የበላይ ተቆጣጣሪ ጀ/ል ሳሞራ የኑስ ሲሆን ከስሩ አንድ ሌላ ለመለስና ለባለቤቱ አዜብ ቅርብ የሆነ ጂኔራል የቤተመንግስቱ የጥበቃ ሀላፊ ሆኖ መመደቡንም የገለፁት ምንጮች መለስ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ካድሬች እንኳዋን ባለማመኑ አዲስ ጦር ማምጣቱ የመፈንቅለ መንግስት ይደረግብኛል ብሎ ስጋት ስለገባው መሆኑ እንዳልቀረ ግምታቸውን የሰነዘሩት የቤተመንግስት ምንጮች ወ/ሮ አዜብ መስፍን ከተወለደችበት አካባቢ ተመልምለው በድብቅ ሰልጥነው የተመደቡ ወታደሮች መሆናቸውንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች መካከል መቃቃር ስላለ አንዱ አንዱን በአይነ ቁራኛ እየተጠባበቁ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው ከቀድሞው በበለጠ የአንድ ወገን የበላይነት ብቻ ሳይሆን የአንድ መንደር ሰች እየተሰባሰቡ የሚዶሉትበት ደረጃ ላይ መደረሱንም ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል፡፡

በሰሜን ከሻዕቢያ ጋር የቃላት ሙግት የገጠሙት የወያኔ የጦር አለቆች ሰሞኑን ምንነቱ ያልታወቀ የታሸገ ኮንተነር በ42 ባለ ተሳቢ ቮልቮ የጭነት መኪኖች ወደ ቀድሞው የምድር ጦር ግቢ ሲያስገቡ መታየታቸውን ከአይን እማኞች ለመረዳት ተችሎዋል።

ጳጉሜ 3 ቀን 2000 ዓ. ም. ከጡዋቱ 2 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ድረስ ሲጉዋጉዋዙ የተስተዋሉት የመከላከያ ባለተሳቢ መኪኖች ታሽጎ የገባው ኮንተነር ምናልባትም የጦር መሳሪያ ሳይሆን እንዳልቀረ የአይን እማኞች ግምታቸውን ሰንዝረዋል።በወቅቱ ኮንተነሩን ጭነው ከታዩት መኪኖች መሀከል የጎን ቁጥር ቪ-056፤ ቪ-080፤ ቪ- 116፤ ቪ-046፤ ቪ-114፤ እንደሚገኙበትም ገልፀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን አዲሱ ለገሰ ረሀብ በሀገሪቱ ሊጠፋ ተቃርቦዋል እያለ በሚለፍፍበት በዚህ ወቅት እንኩዋን በሀገሪቱ ካሉ 600 ወረዳች ውስጥ 144 ያህሉ በከፋ ረሀብ እንደተጠቁና በርካታ ዜጎችም በየቀኑ እየሞቱ መሆኑ ከተለያዩ አካባቢች የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

የወያኔው ቁንጣን የወጠረው ባለስልጣን አዲሱ ለገሰ ከህዝብ በዘረፈው ገንዘብ ፓፒረስ የተባለ እጅግ ዘመናዊ ሆተል በባህር ዳር አስገንብቶ እንደልቡ እየተምነሸነሸ ህዝብ ረንቡ ፀንቶበት እየሞተና ቀዬውን ለቅቆ እየተሰደደ ረሀቡ ሊጠፋ ተቃርቡዋል እያለ መግለጫ መስጠቱ የሀገሪቱዋን ህዝቦች መናቁን ያሳያል ያሉት አንድ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ በሱማሌ ክልል ውስጥ ያለው ረሀብ ግን ከሁሉም የከፋና ስር የሰደደ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በቅርቡ በሱማሌ ክልል ውስጥ ከ ሲ. ኤን.ኤን. አለም አቀፍ ሚዲያ የተላኩ ጋዜጠኞች ወደ ኦጋዴን እንደተጉዋዙና በአካባቢው የደረሰውን ሰብአዊ ቀውስ እንደቀረፁ የገለፁት እኚ ሁ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ በየቦታው ወድቀው የነበሩ የሰውና የከብቶች አስከሬን ተሰብስቦ እንዲቃጠል መደረጉንም ጨምረው ገልፀዋል።

በመከላከያ የጦር ሔሊኮፕተር ኬያለበት አስከሬን ተለቅሞ በጉድጉዋድ ውስጥ እንዲቃጠል እየተደረገ መሆኑን የሚያውቁት የወያኔ ባለስልጣናት ረሀቡ ሊጠፋ ተቃርቦዋል እያሉ መለፈፋቸው በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ያሉት እኚሁ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ አስከሬኖች ተለቅመው እንዲቀበሩ የተደረገው የአለም አቀፍ ሚዲያ የሆነው አልጀዚራ ጋዜጠኞች በመምጣታቸውና እየተሰራ ያለውን ግፍና በደል እንዳያጋልጡ ነው ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ገልፀዋል።

በቅርቡ ድንገት በአካባቢው ተገኝተው የህዝቡን እንቅስቃሴ የተከታተሉት የሲ.ኤን. ኤን. ጋዜጠኞች እንደልባቸው ተዘዋውረው እንዳይቀርፁ የወያኔ ወታደሮች ሲከለክሉዋቸው እንደነበር ያስረዱት ምንጮች አሁንም የአልጀዚራ ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው የተጉዋዙ

ቢሆንም እንደበፊተኞቹ ጋዜጠኞች ተመሳሳይ እጣ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ስጋታቸውን ገልፀዋል።

ሀገር እንመራለን እያሉ በጨበጣ እየተጉዋዙ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ከ10 ቀን በላይ በተለያዩ ቦታች ስብሰባ እያሉ ቢከርሙም ስለረሀብተኛው ወገን አንዲትም ትንፍሽ ሳይሉ ይልቁንም በለመዱት የሀሰት ፕሮፓጋንዳቸው ልማት በሀገሪቱ እየተፋጠነ ነው እያሉ እራሳቸው ተናግረው እራሳቸውን የሚያደምጡ በመሆናቸው ፍፁም ከሰው ልጅ የማይጠበቅ አረመኔ ተግባር እየፈፀሙ ናቸው ሲሉም ለጋሽ ድርጅት መሪች ሲገልጡ ተደምጠዋል።

ለብዙ አመታት በኢትዮጵያ ተሌቭዥን ውስጥ በኦሮሚኛ ፕሮግራም ሲሰሩ የነበሩ ጋዜጠኞች ከስራቸው መባረራቸውን የማስታወቂያ ሚኒስተር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

ከ15 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ተሌቭዥን በኦሮሚኛ ፕሮግራም አዘጋጅነት ሲሰሩ የነበሩ ጋዜጠኞች ያለ አንዳች ክፍያና አበል የተባረሩ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በቅርቡ በሁሉም ክልል የተሌቭዥን ስርጭት በየራሳቸው እንዲሆን በተደረገው መሰረት የኦሮሚያ ክልል የተባለው አስተዳደር የራሱን አዳዲስ ካድሬ ጋዜጠኞችን በመቅጠሩ ነባሮቹን ለማባረር እንደቻለ ገልፀዋል።

ከተክኒሻንነት እስከ ዋና ፕሮግራም ኃላፊነት ደረጃ የነበሩትን ጋዜጠኞች ከስራ ገበታቸው ላይ ያለምንም ክፍያ ካባረረ በሁዋላ ከሀገር እንዳይወጡ በደህንነት ጥብቅ ክትትል እንዲደረግባቸው ከማስታወቂያ ሚኒስትሩ ብርሀን ሀይሉ ተዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ በአሁን ሰዓት ጋዜጠኞቹ ለከፋ ችግር ተዳርገው እንደሚገኙ አስረድተዋል።

ወትሮም መጥጦ መጣል የሚያውቅበት ወያኔ ነባር የኦሮሚኛ ጋዜጠኞችን በተደጋጋሚ ጊዜ የወያኔ አባል እንዲሆኑ ቢያስፈራራቸውም አሻፈረኝ በማለታቸው ምክንያት ለመባረር እንደበቁ የገለፁት ምንጮቹ ህሊናቸውን ሸጠው የሚኖሩትን ሆድ አደር አዲስ ካድሬ ጋዜጠኞችን በምትካቸው የቀጠሩ ሲሆን እነዚህ አዲስ ጋዜጠኞች በተደራቢነት የደህንነት ስራ እንዲሰሩም ትዕዛዝና ኮርስ እንደተሰጣቸው ከምንጮቹ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

በቅርቡ የተሌቭዥን ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ የተመደበው ብርሀን የተባለው የትግራይ ድምፅ የወያኔ ሬድዮ አዘጋጅ የነበረ የህወሀት ነባር ታጋይ ቦታውን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ በርካታ ጋዜጠኞችን ያለ ምንም ምክንያት ያባረረ ሲሆን በመትካቸው የወያኔ አባል የሆኑትን ብቻ በፍሪንላንሰርነት ስም እያስገባ በተሌቭዥን ፕሮግራም አዘጋጅነት ውስጥ እየሰገሰገ እንደሚገኝና አሁንም ጥቂት የማይባሉ ነባር ጋዜጠኞችን ለማባረር በዝግጅት ላይ

መሆኑን ምንጮች አጋልጠዋል::

በመጨረሻም የአማራ ክልል የተባለው የወያኔ አስተዳደር በነጋዴችና በአርሶ አደሮች ላይ የጀመረውን ወከባ እና እንግልት እንደቀጠለበት ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ዘገባ ገለጠ::በደረሰን ዘገባ መሰረት በባህር ዳር ፣ በደሴ ፣በደብረ ማርቆስ ፣ በደብረ ብረሀን እና በሌሎችም የአማራ ክልል ከተሞች ውስጥ በሚገኙ ነጋዴች ላይ ከፍተኛ አመታዊ ግብር ቆልለው እያስጨነቁዋቸው መሆኑን ገልፆዋል::

ከአቅማቸው በላይ እና ያልሰሩበትን ግብር እንዲከፍሉ ተገድደው በርካቶች በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከመሆናቸው የተነሳ አካባቢያቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በትነው ለመሄድ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን የገለፀው ይኸው የደረሰን ዘገባ በአነስተኛ ሱቅ በደረተ አመታዊ ግብር ተብሎ የተጠየቀው ከ6 ሺህ ብር በላይ እንደሆነና ሌሎችም ነጋዴች ላይ የመጣው ክፍያ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን አስረድቶዋል::

አንከፍልም አቅም የለንም የሚሉትን ነጋዴች የንግድ ቦታቻቸው ይታሸጉና ባለቤቶቹም ለእስር እንደሚዳረጉ ማስጠንቀቂያ የተሰጣካቸው በመሆኑ በርካቶች ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው እና መላው ጠፍቶዋቸው እንዳለም የደረሰን ዘገባ አክሎ ገልፆዋል::

አንድ የደሴ ከተማ ነጋዴ እንደገለፁት ከሆነ ይህ ሁሉ ጫና የተቆለለብን በ1997 ዓ. ም. በተደረገው ምርጫ ወቅት በአማራ ክልል ውስጥ አንድም የወያኔን እጩ ባለመምረጣችን የተነሳ ያንን ቁጭት ለመወጣት ታስቦ ነው ያሉት እኚሁ ነጋዴ በቅርቡ ህዝቡ በርሀብ እያለቀ የወያኔ ካድሬች በ1997 ዓ. ም. የመረጣችሁት ተቃዋሚችን በመሆኑ እነሱ ይስጡዋችሁ ፣እነሱ ይርዱዋችሁ እያሉ በችጋርና በችግር ሲያስጨርሱዋቸው እንዳልነበር አሁን ደግሞ ስራው በሞተበትና እነሱ እራሳቸው ንግዱን ተቆጣጥረው ባሉበት ወቅት ያልታሰበና ያልተጠበቀ ሂሳብ ክፈሉ መባሉ ወያኔ የነበረውን ቁጭት ለመወጣት አስቦ ነው ሲሉ እልህ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የደህንነት ባለስልጣናት በሙሉ የ24 ሰዓት ጥበቃ እንዲያደርጉ ከመረጃና ደህንንት ቢሮ የወጣው ትዕዛዝ አመለከተ:: የቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ ጥቃት ሊሰነዘር ይችላል በሚል የወያኔ የመረጃና ደህንነት ክፍል ባለስልጣናት በ24 ሠዓት ተከፋፍለው ጥበቃ እያደረጉ መሆኑን የገለፀው ሾልኮ የደረሰን ዘገባ በተለይ የሱማሌ አክራሪች በቦሌ አወሮፕላን ማረፊያ ላይ በሚወጡ እና በሚገቡ የወያኔ ባለስልጣናት ላይ አደጋ ያደርሳሉ ተብሎ ስጋት ስለገባቸው መሆኑን ጨምሮ አስረድቶዋል::

የበታች ሰራተኞቻቸውን ያላመኑት የወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣናት እራሳቸው ስራ ተከፋፍለው እየጠበቁ ሲሆን ለበታቾቻቸው ሳይነግሩ ይህን ማደረጋቸው ምን ተከስቶ

ይሆን? ሲሉም የሚጠይቁ ሰራተኞች በርካቶች ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ፖሊስ ስር የሚገኙ የደህንነት ክትትል ሰራተኞች ከመስከረም 7 ቀን እስከ መስከረም 8 ቀን 2001 ዓ.ም.ለሁለት ቀናት ግምገማ ያካሄዱ ሲሆን በዚህ ግምገማ ላይ ለጊዜው ስሙ ያልተገለፀ የወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣን ተገኝቶ «እናንተ ከህዝብ ጋር በጥቅም የተሳሰራችሁ በመሆኑ ስራውን ትታችሁታል ፡፡ይህ ደግሞ ለስራችን እንቅፋት ይፈጥርብናል» በማለት ለማስፈራራት ቢሞክርም ተሰብሰቢ ደህንነት ሰራተኞቹ ግን «ከህዝብ ተነጥሎ ስራ ውጤቱን ያየነው በመሆኑ ያንን ሁለተኛ ልንደግመው አይገባንም ስለዚህ ከህዝብ ጋር መሆን ግድ ይለናል »በማለት አፀፋዊ ምላሽ ሰጥተው እንደተለያዩ ሾልኮ የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አብራርቶዋል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለ3 ሰዓታት የፈጀ ስብሰባ ሜክሲኮ በሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ መደረጉ ታወቀ፡፡ወርቅነህ ገበየሁ የተባለው የወያኔ ሹም ባለስልጣናቱን ሰብስቦ እንዳነጋገራቸው የገለፀው ሾልኮ የደረሰን ዘገባ «ከፍተኛ ስራ ከፊታችን የተደቀነ በመሆኑ ሌት ተቀን ልንሰራ ግድ ስለሚለን ሁላችንም ተዕዛዙን ለመፈፀም ዝግጁ ሆነን መቀመጥ አለብን» ሲል በሚስጥር በተደረገው ስብሰባ ላይ የገለፀ መሆኑን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

በደህንነት እና በፖሊስ ክፍሉ ውስጥ እየተደረገ ያለው ጥበቃና ትርምስ ሁኔታው በግልፅ ባይታወቅም ምናልባትም በወያኔ ባለስልጣናት ውስጥ የተጀመረው ሽኩቻ አይሎ መጥቶ ይሆን? ሲሉም የሚጠይቁ በርካታ ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡